# የወያኔ ሴራ
# አየለ ጫሚሶና ተመስገን ዘውዴ በአገር ቤት አንዳርጋቸው ጽጌና ብርሃነ መዋ በውጭው ዓለም የተለጣፊው ቅንጅት መሪዎች

ቅንጅት በኢትዮጵያ ሕዝብ ምርጫ ወያኔን በአሸናፊነት ከዘረረ ከግንቦት 1997 በኋላ የተደናገጠው ወያኔ አባላቱንና ደጋፊዎቹን በአሰቃቂ ሁኔታ ገድሎና አቁስሎ፣ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩትን ወጣቶች በየእስር ካምፑ አጉሮ ሲያሰቃይ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመረጣቸውን የፓርላማ አባሎችና የአገር መሪዎች በሀሰት ወንጅሎና በግፍ አስሮ ሲያንገላታ፣ ለእውነትና ለዲሞክራሲ ሲታገሉ የነበሩትን ጋዜጠኞች፣ የሲቪክና የሙያ ማህበራት መሪዎች፣ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎችን በወህኒ እያማቀቃቸው ከፊሉም ስደተኛ ሆኖ ሲንከራተት የወያኔ ተላላኪዎችና ሆድ አደሮች ወያኔያዊ ተልዕኳቸውን በያሉበት እየፈጸሙና ጌቶቻቸውን እያስደሰቱ ይገኛሉ።

ጀግኖች መሪዎቻችን የሕዝብን አደራ ጠብቀውና አክብረው ከፍተኛ መስዋዕትነት ሲከፍሉ ከሃዲዎችና ሆድ አደሮች እነልደቱ አያሌው፣ አየለ ጫሚሶና ተመስገን ዘውዴ ምን ዓይነት ሥራ እየሰሩ መሆናቸውን ድፍን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያውቀው ነገር ስለሆነ የእነርሱን ማንነት መናገር አስፈላጊ አይሆንም ምክንያቱም ሥራቸው ይናገራልና።

ከሃዲው ልደቱ አያሌው ከምርጫው በፊት የተከበሩና አንቱ የተባሉትን ጀግኖቻችንን አንድ ሰሞን የዕድሜ ክልል በመፍጠር ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው መታገላቸውን በማናናቅ የጡረታ ጊዜ ማሳለፊያ ቦታ እንዳደረጉት በመቁጠር የድፍረትና የብልግና አነጋገር ሲያሰማን ነበር። የአንድ ሰሞን ዝነኛው አቶ ልደቱ ብዙ ብዙ ነገርም ሲናገር ተደምጧል። ዛሬም ያንን ፈለግ ተከትለው መሪዎቻችን እስር ቤት ተረስተው እንዲቀሩ የሚፈልጉ መልዕክተኞች ተግተው የሚሰሩት የመሪነቱን ቦታ "ለአዲሶቹና ለወጣቶቹ" መሰጠት አለበት በሚል ፈሊጥ ሌሎች መሪዎች እነርሱ ሊመርጡልን ይፈልጋሉ።

እነ አየለ ጫሚሶና ተመስገን ዘውዴም ወያኔያዊ ተልዕኳቸውን ለማሳካት ተለጣፊ ቅንጅትን በመፍጠር ደፋ ቀና ሲሉ፣ የተለጣፊ ቅንጅት ስብሰባ ሲጠሩ፣ የተለጣፊ ቅንጅትን መሪ መረጥን በማለት ድራማ ሲሰሩ ቆይተዋል። ወያኔ ያገር ቤቱ ትግሉን የማዳፈንና የማዳከሙ ስራው በተለጣፊ መሪዎች መንገድ የያዘለት ሲመስለው የሚቀጥለው ፕሮጀክት የውጭውን ትግል መቆጣጠርና መከፋፈል፣ ማዳከምና የራሱን ተለጣፊ ድርጅቶች በስውር ተልዕኮ ባላቸው ሰዎች አማካኝነት ማቋቋም ነበር።

እንደሚታወቀው ሁሉ የውጭው ክፍል ትግል ወያኔን ጤና እየነሳው ስላስቸገረው የሚቆጠጣጠርበትን መንገድ ማስላት ከጀመረ ሰንበት ብሏል። ያዘጋጃቸውን ሰዎች ጊዜውን ጠብቆ በማሰማራቱ ፕሮጀክቱ በመጠኑ የሰራለት ይመስላል። ሆኖም ግን ትግሉን ይጎትተውና ትንሽ ያዳክመው እንደሆን እንጂ አያጠፋውም። አይቀለብሰውም።

ለመሆኑ ዛሬ በውጭ አገር ያሉት የቅንጅት ደጋፊ ድርጅቶች መከፋፈልና መዳከም እንዴት ሊከሰት ቻለ? ቅንጅት ኢንተርናሽናል የተባለውን እንዴትና ማን ፈጠረው? መሪዎቻችንስ ከቃሊቲ በእርግጥ እነዚያን 6 ሰዎች በስም መርጠውና ሾመው ቅንጅትን እንዲመሩ ወክለዋልን? ካልወከሉ ሜይ 14 ቀን 2006 ከቃሊቲ መጣ የተባለው የኢሜይል ሹመት ከማን ተላከ? በማን በኩል መጣ? የሚሉትን ጥያቄዎች መልስ ማግኘት አለባቸው።

አለበለዚያ ምንጩንና መነሻውን ካልያዝን ዛሬ በየቀኑ አካሄዳቸውና ሥራቸው እየተቀያየረ ስላስቸገረ በውጭ ያለው ሕዝብ ትክክለኛ ግንዛቤ ማግኘት አይችልም። ያ ደግሞ ትክክለኛ አቂም እንዳይዝ እንቅፋት ሆኖ ግራ መጋባትን፣ ከትግሉ መሸሽና ማፈግፈግን ያስከትላልና ያንን ለማሳወቅ እውነቱ ተደጋግሞ መነገርና መታወቅ አለበት።

ሜይ 14 እና 15 የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች በሜሪላንድ የሁለት ቀን ስብሰባ ያካሂዱ ነበር:: ብዙ አጀንዳዎች ላይ ተወያይተው የሰሜን አሜሪካኑን የድጋፍ ደርጅቶች የሚመሩ 15 አባላት ያለት የመማክርት ሸንጎ መርጠው ወደ ሥራቸው ለመሰማራት በሞቀ የሥራ መንፈስ ውስጥ እያሉ የሰሜን አሜሪካው የድጋፍ ድርጅቶች ሊቀመንበር ሻለቃ ዮሴፍ ያዘው ካገር ቤት አመራር ጋር ቀጥታ ግንኙነት እያላቸው እሳቸው ሳያውቁት የሹመት መልዕክት መጣ የተባለው በጸሀፊው በአቶ ብርሃነ መዋ በኩል ነበር:: ይህም ያልተለመደና ፕሮቶኮል ያልጠበቀ ነበር:: የሆነው ሆኖ ጸሐፊው ከቃሊቲ የመጣ ደብዳቤ አለ ስላሉ ጉባዔው ደብዳቤው እንዲነበብ ወስኖ ተነበበ:: ይዘቱ ቃሊቲ ያሉት መሪዎች የስድስት ሰዎችን ስም ይዘረዝርና የቅንጅትን አመራርና ሙሉ ሥልጣን እንዲመሩ አስረክበናል ይላል:: ለሁሉም አዲስ ነገር ስለሆነ ግራ ተጋቡ:: እንዴት ሊሆን ቻለ? እርግጠ ኛነቱ በምን ይታወቃል? የመሳሰሉት ጥያቄዎች ተነሱ:: መጨረሻ ላይ ሊቀመንበሩ ሻለቃ ዮሴፍ ይኸንን ነገር ለመቀበል በጣም ስለሚከብደኝ ነገሩ መጣራት አለበት ብለው ቤቱም ያንን ሀሳብ በመደገፍ ጉዳዩ በከፍተኛ ምስጢር ተይዞ እስኪጣራ ድረስ ለሕዝብም ሆነ ለሚዲያ እንዳይነገር ብሎ ወስኖ ተበተነ:: ይህ የሆነው ሜይ 15 ቀን 2006 ሲሆን በሶስተኛው ቀን ይኸው ይጣራ የተባለው ጉዳይ በኢትዮጵያ ሪቪው ድኀረ ገጽ ላይ በይፋ ወጣ:: ከዚያ በኋላማ ድኀረ ገጾች ሁሉ ተቀባብለው ቅንጅት ኢንተርናሽናል ተቋቋመ ተብሎ የአንድ ሰሞን ዜና ሆነ::

የድጋፍ ደርጅቶች አባላት የነገሩን አደገኛነት ተገንዝበው ቅንጅት የተፈጠረውም ያለውም መኖርም የሚገባው ኢትየጵያ ውስጥ እንጂ ስደተኛ መሆን የለበትም፣ መሪዎቻችንም ቅንጅት ስደተኛ እንዲሆን አይፈቅዱም በማለት የጦፈ ክርክር ተካሄደ::

ሁኔታው ያስፈራቸው እነ አቶ ብርሃነ መዋ እቅዳቸው እንዳይበላሽ ሌላ መግለጫ በአምስተኛው ቀን አወጡ:: ቅንጅት ከኢትዮጵያ አይወጣም መሪዎቹም ቃሊቲ ያሉት ናቸው የሚል ቢሆንም በመግለጫው ውስጥ ቅንጅት ኢንተርናሽናል በየአህጉሩና በየከተማው የፓርቲ ተጠሪዎችን ይሰይማል ማንኛውም የድጋፍ ደርጅት ከአሁን በኋላ ከአገር ቤት ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ተቋርጦ ከቅንጅት ኢንተርናሽናል ጋር ብቻ ይሆናል አለ:: ስድስቱ ሰዎች ለማንም ተጠሪ አይሆኑም:: እንዲህ እያሉ ሁኔታውን ለመቆጣጠር ከሚያስቸግርበት ደረጃ ላይ ያደርሱታል:: አስቀድመው የተዘጋጁበት ነገር ስለነበር በየከተማው አንድና ሁለት ሰዎችን በመመልመል የእነርሱ ዓላማ ደጋፊ ማድረግ ጀመሩ:: ትንሽ ቆይቶ እነ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በየድጋፍ ድርጅቶች በደርግ ጊዜ እንደነበረው የኢሰፓ አባልነት አይነት መጠይቅ በመላክ ስለ እያንዳንዱ ድርጅት መሪዎችና አባላት የግል መረጃ ለማሰባሰብ ሞከሩ:: ለትንሹም ለትልቁም ነገር መግለጫ ማውጣት እና ቅንጅት ኢንተርናሽናልን ለማስተዋወቅና ሕጋዊ ሽፋን ለመስጠትም ሞከሩ:: በዚህን ጊዜ ሁኔታው ከመጀመሪያውም አጠራጣሪ የነበረው ነገር አሁን ደግሞ ድርጅቶችን ሁሉ ለመቆጣጠር የሚያደርጉት ሩጫ ያሳሰባቸው የድጋፍ ድርጅቶች መሪዎችና አባላት መጠየቅ እና መቃወም ጀመሩ:: የጠየቃቸውና የተቃወማቸው ላይ የስድብ ውርጅብኝ አወረዱበት::

ነገሩን በውይይትና በዝግ ስብሰባዎች ለመጨረስ የተደረጉ ጥረቶች ሁሉ መፍትሔ በማምጣት ፈንታ አላስፈላጊ ጭቅጭቅና ንትርክ ስለፈጠሩ በቅን ልቦና ሲደግፍ የነበረው ደጋፊ ሁሉ ማመንታትና ግራ መጋባት ይታይበት ጀመር::

እነ አቶ ብርሃነና አቶ አንዳርጋቸው አዲሶቹ የቅንጅት መሪዎች ሆነው መግለጫ መስጠት፣ ቃለ መጠይቅ ማካሄድና በየከተማው እየሄዱ የራሳቸውን ስራ ማካሄድ የፓርቲ አባል መመልመል ይጀምራሉ:: ግልጽ የሆነ የመስመር ልዩነት እየታየ ሲመጣ አስቀድመው የሚዲያ ማሰራጫዎችን በመያዝ ለብዙ ጊዜ ሲታገሉ የቆዩትን ጠንካራ ሰዎች ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ ይጀምራሉ:: አመራር ላይ ያሉት መምራት አይችሉም፣ ስራ አይሰሩም፣ገንዘብ ተዘረፈ ወዘተ.... ዘመቻቸውን ተያያዙት:: ትልቅ ሴራ እንደተሸረበና እየተፈጸመ መሆኑን ሁሉም የድጋፍ ድርጅቶች በመረዳታቸው በኦገስት 2006 አስቸኳይ ስብሰባ እንዲካሄድ ጠየቁ:: ስብሰባውን ለማጨናገፍ ያላደረጉት ሙከራና ጥረት አልነበረም::

ጥቂት ሰዎች ስብሰባ አያስፈልግም በሚል ፔቲሽን ፈርመው አስገቡ። በአብዛኛው የድጋፍ ድርጅቶች ድምጽ ስብሰባው እንዲካሄድ ተወሰነ።

ሌላ ተንኮል ደግሞ ተጠነሰሰ። አሁንም ጥቂት ሰዎች ሆነው በቴሌኮንፈረንስ ስብሰባው የሚደናቀፍበትን መንገድ ዶለቱ። አንዱ ለምን የሰሜን አሜሪካው ሊቀመንበር ገንዘብ አጠፉ ብለን አንከስም እና ሌሎቻችን ያንን በመጠቀምና ሊቀመንበሩን በማዋረድ ከኃላፊነት ቦታቸው አናወርዳቸውም ተባባሉ። ይህንን ለማድረግ አመቺ የሆነው ከሁለት ወር በፊት ኦዲተር ሆኖ የሰራውን ሰው በሜይ 2006 ስብሰባ ላይ የገንዘብ አያያዙና አሰራር በመልካም እጅ ነው ብሎ ቤቱ በጭብጨባ ሪፖርቱን ደግፎ የተለየው ሰው ከሁለት ወር በኋላ ለዚያውም ከኦዲተርነቱ ተሰናብቶ የነበረውን ሰው አንተ ሻለቃ ዮሴፍ ገንዘብ አባክነዋል ብለህ ሪፖርት አድርግ እኛ ይህንን ካጠፉ ከሊቀመንበርነታቸው እናወርዳቸዋለን ተብብለው ወሰኑ። ይህ ሁሉ ተንኮል በቴሌኮንፈረንስ ሲሸርቡ የቴሌኮንፈረንሱን ስብሰባው የተሳተፉ ግለሰብ የውይይቱ አርዕስት ተቀይሮ አድማ መሆኑ ሲያሳስባቸው ጊዜ ማስረጃ መያዙ ይጠቅማል በማለት ሴራውን በድምጽ መቅጃ መቅዳታቸውን አላወቁም። ለወንጀላቸውና ለሴራቸው ትልቅ ማስረጃ መያዙን ሳያውቁ ወደ ስብሰባው ገቡ። ስብሰባውን ለማደናቀፍና ለመበጥበጥ ያላደረጉት ጥረት የለም። የቅንጅት ኢንተርናሽናል ደጋፊዎች ማለትም ብጥበጣውን ለማካሄድ ያቀዱት ሰዎች በስብሰባው ላይ የነበራቸው የሥነሥርዓት ጉድለት እጅግ አሳፋሪ ነበር። የስብሰባው ሂደት በሙሉ በካሜራ የተቀረጸ ስለሆነ በቂ ማስረጃ አለ። እንዲያውም በስብሰባው ላይ ማንም ያላሰበውንና ያልጠበቀውን ምስጢርም አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ አመለጣቸው። የአንዱ የድጋፍ ድርጅት አባል የሆኑ፡ "ይህን ከቃሊቲ መጣ የተባለው ሹመትና ደብዳቤ በምንም ዓይነት የመሪዎቻችን ቃል አይደለም። መሪዎቻችን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጂ ሕዝቦች አይሉም ያ ቃል የወያኔ መጠቀሚያ ቃል ነው። ከሆነስ ሆነና ቃሊቲ ያሉት የቅንጅቱ ሊቀመንበር እነዚህን ስድስት ሰዎች በስም ከወከሉ በጣም የሚያውቁትን የአንዱን ሰው ስም እንዴት ስሙን አሳስተው ሾመናል አሉ ምክንያቱም ለብዙ ጊዜ ይተዋወቃሉ እና ስሙን መሳሳት አይችሉም" ብለው ሲጠይቁ አቶ አንዳርጋቸው ሳያስቡት "ስህተቱ ወደ አማርኛ ሲተረጎም ነው" በእንግሊዝኛው በትክክል ጽፌ ነው የላክሁት" አሉ። እውነቱ ሳያስቡት አመለጣቸው። ተሰብሳቢው በሙሉ ምስጢሩ ሳይታሰብ በመውጣቱ ተንኮሉን ተረዳው። አይ የሀሰት ነገር ጥርጣሬው ትክክል ሆነ። የጉባዔው ተካፋዮች ደብዳቤው ከለንደን ዋሽንግተን ከዋሽንግተን አዲስ አበባ ከአዲስ አበባ ደግሞ ተጽፎ እንደተላከ መልዕክት ዋሽንግተን በአቶ ብርሃነ መዋ ተዋናይነት እንደቀረበ ተረዳ። እንዲህም አድርጎ ሹመት የለ።

የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌና የአቶ ብርሃነ መዋ 14 ዓመት ሙሉ ጸረ ወያኔ ትግል አካሂደው የማያውቁ ሰዎች እንዲያውም ከወያኔ ጋር የሰሩና የኖሩ ሰዎች በድንገት በፓራሹት ወርደው እራሳቸውን የቅንጅት መሪዎች አደረጉ። የቅንጅት መሪዎች እኮ ፕሮግራማቸውን ለሕዝብ አቅርበው፣ ሕዝብ አደራጅተው፣ ታግለው አታግለው ለምርጫ ካበቁ በኋላ 26 ሚልዮን የኢትየጵያ ሕዝብ ወጥቶ መርጧቸው ነው መሪ የሆኑት። ታዲያ በምን ሂሳብ ነው እነዚህ ሰዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይመርጣቸው መሪዎቻችን ሳይሰይሟቸውና ሳይወክሏቸው በመሪዎቻችን ስም ይህንን ስራ የሚሰሩት?

ለመሆኑ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ማናቸው? አዎን አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን የአዲስ አባባ ሕዝብ ያውቃቸዋል። ወያኔ አገሪቱን ሲቆጣጠር በየቦታው ያሉትን ካድሬዎችና ደጋፊዎቹን ሰባስቦ ሚኒልክ ቤተመንግሥት ሲገባ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቃውሞውን ሲያሰማ ከለንደን ሮጠው ከነመለስ ዜናዊ ጋር የሰሩ የወያኔ ባለሥልጣን ነበሩ። በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ለሁለት ዓመት ተኩል ያህል በምክትል ከንቲባነት ወይም ተመሳሳይ ደረጃ ባለው ኃላፊነት የሰሩ አገር ሲገነጠል፣ ሕዝብ በጎሳ ሲከፋፈል፣ ሲካለል፣ አገር ሲጠፋ አብረው ያጠፉ ነበሩ። በ1985 ዓ.ም የአማራ ሕዝብ ከየት ወዴየት የሚለው የወያኔን የጎሳ ፖለቲካ የሚያራምድ አቂማቸው ያንጸባረቁበት፣ የኢትየጵያን ታሪክ ክደው በአንድ መቶ ዓመት የወሰኗት፣ እያንዳንዱ በጎሳውና በብሔሩ ሲደራጅ ነው እድገትና ልማት የሚመጣው ብለው የመለሰን ዜናዊን ስራ ሲሰሩ የከረሙ ሰው ያሰቡትን ያህል ሹመትና ሽልማት ስላልተሰጣቸው ከወርቅ ዘር አለመገኘታቸውንም ዘንግተው ኖሮ በዚያ ቅር ተሰኝተው በሹመት አነሰኝ ምክንያት ወደ ለንደን ተመለሱ። እስከ 1997 ምርጫው ሊቃረብ ሶስትና ሁለት ወር እስኪቀረው አንድም

ቀን ወያኔን ተቃውመው የማያውቁት ሰው ግርግር ለሌባ ያመቻል እንዲሉ በምርጫው ግርግር አዲስ አበባ መጡና ቅንጅትን ለመርዳት ጉድ ጉድ ማለት ጀመሩ:: ከምርጫው በኋላ በቅንጅት ደጋፊነት ሳይሆን ወያኔን የተቃወሙ ለመምሰልና በተቃዋሚው ጎራ ቦታ ለማግኘት በጻፉት መጽሐፍ ሳቢያ በሰኔ 1997 ለሁለት ነው ለሶስት ሳምንት ታስረው ሌሎቹ መከራቸውን ሲያዩ እሳቸው ወደ ለንደን አቀኑ:: የመታሰሩ ድራማ አቶ ልደቱ አያሌውም ታስረው እንደ ማንዴላ እስኪቆጠሩ ድረስ ዝና ፈጥሮላቸው ነበር:: አሁንም ተመሳሳይ ድራማ እንደተሰራ ጥርጥር የለንም:: አቶ ልደቱም ተገረፉ ተደበደቡ ተብለን ተነግሮናል እንዲያውም እስር ቤት ሲገቡ ልብሳቸውን ቀዳደው የተገረፉ ለማስመለስ በባዶ እግራቸው ሲገቡ አብረው ያሉት እስረኞች አገላብጠው አይተዋቸዋል አንዳችም ጠባሳ ወይም የመገረፍ ምልክት በሰውነታቸው ላይ አልነበረም:: በሚዲያው ግን በጣም እንደተገረፉ ነበር የተዘገበው:: አቶ አንዳርጋቸውም አንድ አይናቸው ለመጥፋት እስኪያሰጋው ድረስ ተመትተው ነበር ተብሏል:: እውነቱን የሚያውቁት እሳቸውና ፈጣሪ ብቻ ነው:: በአንድ ጊዜ ዝነኛ ሆኑ:: እረ ለመሆኑ የኢትዮጵያ ሪቪው ዌብ ሳይት አዘጋጅ አቶ ኤልያስ ክፍሌ ከዓመት ተኩል በፊት አዲስ አበባ ላለው የቅንጅት አመራር የተማጽኖ ጽሑፍ በድኅረ ገጹ ላይ ማውጣቱ ያጋጣሚ ነው ወይስ ቀድሞ የታሰበ የተቀነባበረ ዘመቻ? የአትዮጵያ ሪቪው አቶ ኤልያስ ክፍሌ ያወጣው ጽሑፍ የሰሜን አሜሪካውን ትግል ለመምራት ብቃትና ጥራት ያላቸው ሰው አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ስለሆኑ እሳቸው መምራት አለባቸው ይል ነበር:: መሪዎቻችን ያኔ አልታሰሩም:: በዚያን ጊዜ ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶችም ሆነ አመራር ስለ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የሚያውቀው ምንም ነገር አልነበረም:: ለካስ አሰቀድመው ነበር ለመሪነት የታጩት:: የኢትዮጵያን ሪቪው አዘጋጅ የአቶ ኤልያስ ክፍሌ ተልዕኮ ምን እንደሆነና ለማን እንደሚሰሩ ሕዝብ አሳምሮ ያውቃል:: የማታውቁም ካላችሁ ልታውቁ ይገባል:: ምኞቱና ጥቆማው ሰምሮለት ከአንድ ዓመት ተኩል በኋላ "መሪዎቻችን ከቃሊቲ በኢሜይል" ሲሾሙ ኢትዮጵያ ሪቪው መልስ አገኘ:: የሚገርም ነው::

አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በአውሮፓ ያለውን የቅንጅት ድጋፍ ካዳከሙና ራሳቸው ያዘጋጇቸውን ሰዎች በለንደንና በሌሎችም ከተሞች በአድማና አስርጎ በማስገባት ስራቸውን ካከናወኑ በኋላ የሰሜን አሜሪካ ጓዳቸውን አቶ ብርሃነ መዋን ለመርዳት ወደ ዋሽንግተን ብቅ ማለት አዘወተሩ:: አቶ አንዳርጋቸው ውጭ አገር እንዳለነው ስደተኞች ኑሮን ለመቂቂም በሥራ ደፉ ቀና አይሉም:: እድለኛ ናቸው:: ከአውሮፓ አሜሪካ ከአሜሪካ አውሮፓ በየጊዜው ይመላለሳሉ:: ከርመው ደግሞ ይሄዳሉ ይመጣሉ:: ዝናቸው ከመታወቅም አልፎ በአንዳንድ ደካሞች ዘንድ መመለክ ተጀመረ:: አዎን ሃሳባቸውና ሥራቸው በመጠኑ ሰምሮላቸው ነበር ሕዝብ ማንነታቸውን አውቆ መጋለጥ እስኪጀምሩ ድረስ:: እውነት ብቅ አለች:: ማንነታቸውንና ሥራቸውን አጋለጠች:: አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ሌላም ብዙ የሰሩት ስራ አለ የሌሎችን ሰዎች ደህንነት ለመጠበቅ በማሰብ በዚህ ጽሑፍ ለማቅረብ ባይቻልም ወቅቱን ጠ ብቆ ይወጣል:: ተደብቆ የሚቀር ነገር የለም:: ማንነታቸውን ያላወቁ ሰዎች ባለማወቅ ቢታለሉም አሁን እውነቱ እየታወቀ ነውና ከእውነት ጋር መቆምና ቀናውን መንገድ መያዝ ይኖርባቸዋል:: ወያኔ የሚልካቸው ሰዎች በደንብ የሰለጠኑበት ነገር ቢኖር ሲጋለጡም ማፈር የለም አይናቸውን በጨው አጥበው በሌላ መንገድና ዜዴ ደግሞ ሊያታልሉ ይሞክራሉ::

አቶ ብርሃነ መዋ ለ14 ዓመት በአገር ቤት ሲኖሩ አንድም ቀን በጸረ ወያኔ ትግል እንቅስቃሴ ያልነበሩ፣ የወያኔ የአገር ማጥፋት ፖሊሲ ተስማምቲቸው እንዲያውም በወያኔ ዘመን ኑሮ ተመችቲቸውና ሀብታምና ሚሊየነር ከሚባሉት ነጋዴዎች አንዱ ለመሆን የበቁ፡ የንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት የነበሩ እንደሆነ ሲታወቅ ለግንቦቱ ምርጫ ጥቂት ወራቶች ሲቀር የመንግሥት ታክስ አልከፈሉም ተብሎ በወያኔ ክስ ቀረበበኝ በማለት የታክስ ገንዘብ መክፈል አቅቲቸው በ15ኛው ቀን በኬንያ በኩል አድርገው አሜሪካ ገቡ:: ከዚያ በፊት የተቃዋሚ ድርጅት አባልም አልነበሩ:: የቅንጅት ስሙን እንጂ በተግባር አንድም ቀን ሲሳተፉ ድምጻቸው አልተሰማም:: ታዲያ አሜሪካ ከመጡ ከቂት ወራቶች በኋላ የቀስተ ደመና ድርጅት ደጋፊ ሆነው መስራት ጀመሩ:: በአጭር ጊዜ ዝነኛ ሆነው የትግሉ መሪ ለመሆን በየቃለ መጠይቁ በየሰልፉ ድምጻቸውን ማሰማት ጀመሩ:: ከሰሜን አሜሪካው የድጋፍ ድርጅት አመራር ጋርም መስራትም ቀጠሉ:: የሌሎች ድጋፍ ድርጅት ተመራጮች የሚያገለግሉት በነጻ ቢሆንም አቶ ብርሃነ መዋ ግን እስከ አገስቱ ስብሰባ ድረስ ገንዘብ እየተከፈላቸው ነበር ሲሰሩ የቆዩት:: ሥራቸውን ግን በውስጥ ለውስጥ እንደ አቶ

አንዳርጋቸው ጽጌ እየሰሩ የራሳቸውን ሰው ሲያዘጋጁና ሴራ ሲዶልቱ ቆይተው የኢሜይል መልዕክት አቀባይና "ከስድስቱ ተሿሚዎች" አንዱ ለመሆን በቅተዋል። ወዲያውኑ ራሳቸውን የቅንጅት አንተርናሽናል ሴክሬተሪ ጄኔራል አሉ። ሹመት ያዳብር። መግለጫ በመግለጫ ሆንን። ራሳቸውን በሚገባ አስተዋወቁ። በየከተማው የፓርቲ ምልመላ ማካሄድ ጀመሩ። ይህ ሁሉ የሆነው በቃሊቲ መሪዎቻችን ስም ነበር።

ሀሰት ምን ጊዜም ለጊዜው ትገናለች እንጂ አትቆይምና ከጥቂት ወራት በኋላ ከእውነተኛ መሪዎቻችን ማንንም በስም መርጠው እንዳልሾሙ የሚገልጽ ግልጽ መልዕክት መጣ። ወዴት ይግቡ? መንገድ መፈለግ አለበት እውነቱን ለመደበቅም ውዥንብር ፈጠሩ። በከፍተኛ ደረጃ የስም ማጥፋት ዘመቻቸውን አጧጧፉት። መከፋፈል ተፈጠረ። ቃሊቲ ያሉት መሪዎቻችን በውጭ አገር እየተደረገ ያለውን ሁኔታ ተረዱ። በጣም አዘኑ። ትግሉንና ድርጅቱን ማዳን እና ከወያኔ ሰርጎ ገቦች መጠበቅ እንዳለብን በማሳወቅ ግልጽ መልዕክት ላኩ። ማንም ግለሰብ ከትግሉ በላይ እና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎትና ጥቅም በላይ መሆን አይችልምና አስቸኳይ እርምጃ እንዲወሰድ መመሪያ ከቅንጅቱ ሊቀመንበር መጣ። የሰሜን አሜሪካው ተጠሪ ጽሕፈት ቤት በመመሪያው መሰረት ውሳኔ ወስኖ መግለጫ አወጣ። አቶ ብርሃነ መዋና አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ታገዱ ቅንጅት ኢንተርናሽናልም እንዳይንቀሳቀስ ታገደ። ትክክለኛና ወቅታዊ እርምጃ ነበር። ብዙዎቹ እርምጃው ዘገየ በመዘግየቱም ብዙም ጉዳት አደረሰ ይላሉ። እውነት ነው።

ሌላው የሚገርመው ከቅንጅቱ መሪ ከክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል የመጣውን መመሪያና መልዕክት ላለመቀበል በማናናቅ ይህ የአቶ ኃይሉ ጽሑፍና ፊርማ አይደለም በማለት ሽምጥጥ አድርገው ካዱ። ቢሆንስ? ማለትም ጀመሩ። ምን ለማለት እንደተፈለገ ግልጽ ነው።

የሰሜን አሜሪካ ተጠሪ ጽሕፈት ቤት የሰጠው ውሳኔና መግለጫ አልገባቸው እንደሆን አይታወቅም የሌባ ዓይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ ይላል ተረቱ መታገዳቸው እየተነገራቸው የታገዱትና የተባረሩት ሰዎች መልሰው የሰሜን አሜሪካ ሊቀመንበሩን ሻለቃ ዮሴፍ ያዘውን ቅንጅት ኢንተርናሽናል ከሥልጣናቸው አግዷል ብለው አይን ያወጣ መግለጫ አወጡ። በሶስተኛው ቀን ሐሙስ ቃሊቲ ያለው አመራር "ቅንጅት ኢንተርናሽናል የወሰደውን ውሳኔ በመደገፍ መስማማቱን ገለጸ" ብሎ ቃል አቀባያቸው ኢትዮጵያን ሪቪው እና ኢትዮ ሚዲያ ፎረም አሰሙን። የቃሊቲ የመልስ ፍጥነት አስገረመን። እሮብ ወይም ሐሙስ ቃሊቲ ያሉት መሪዎችን መጠየቅ አይቻልም ለነአቶ አንዳርጋቸውና ብርሃነ መዋ የሚሳናቸው የለምና ውሳኔያቸውን በፓራሹት ልከውት ይሆን ከእስረኞች መጠየቂያ ቅዳሜና እሁድ በፊት ከቃሊቲ መልሱን ያገኙት? ሁሉ ነገር በፍጥነት መስራት ሊኖርበት ነው አለበለዚያ እውነቱ እየወጣ እየተጋለጠ መሄዱን ስለተገነዘቡ በመቻኮልና በሩጫ የሰሩትን ስህተት ለመገንዘብ እንኳን ስላልቻሉ በሐሙስ ቀን አሰሙን። ያስቃል። የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል አሉ የሚለውን አባባል በተግባር አሳዩን።

የሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ስብሰባ በዴንቨር ኮሎራዶ ሲካሄድ እነርሱም ሕጋዊ ያልሆነውን ስብሰባ በሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ስም ጥቂት ተከታዮቻቸውን በመያዝ በአትላንታ አደረግን አሉ። በዴንቨር ኮሎራዶ ግን ከ20 በላይ የድጋፍ ድርጅቶች ተሳትፈዋል።

አቶ አንዳርጋቸው ጽጌና አቶ ብርሃነ መዋ በየፓልቶኩ ተዋናይ እንግዶች ሆኑ ዝናቸው በፓልቶኩ ዓለም ገነነ፣ ተወደሰ፣ ተመለከበት። እነርሱን የተናገረ ሰው ተኮነነ፣ ተወገዘ፣ ወያኔ ተባለ፣ ገንዘብ ዘረፈ ተባለ፣ አምባገነን ሆነ ተባለ ምን ያልተባለው ነገር አለ። የቅንጅት እውነተኛ መሪዎች ተረስተው በአንዳርጋቸውና ብርሃነ መዋ ተተኩ።
አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ከ60 ዎቹ የላዕላይ ምክር ቤት አባል አንዱ ነኝ ብለው በሬዲዮና በስብሰባ ዋሽተውን ነገሩን ስናጣራ ስማቸው ከ60ዎቹ መካከል የለበትም። ቅሌት ነው። እንደዚህ ዓይነት የሚዋሽ ሰው ነው የቅንጅት መሪ የሚሆነው?

አሁን ይህን ያህል ፍንጭ ስለ ቅንጅት ኢንተርናሽናል መሪዎችና አመጣጥ ከተገለጠ ቀጣዩ ስራቸው ምንድነው? የሚለውን እንመልከት።

በተለየዩ ትላልቅ ከተሞች የሚያውቋቸውን ማለትም በስራ ዓለም፣ በትምህርት ቤት፣ በስውር ተልዕኮ ስራ እንዲሁም ግራ በተጋቡና ሳያውቁ በተሳሳቱ ግለሰቦች አማካኝነት በየድጋፍ ድርጅቱ መከፋፈልና መለያየት እንዲፈጠር እያደረጉ ሲሆን፤ በአንዳንድ ቦታ የፓርቲ አባል እየመለመሉ ከድጋፍ ድርጅቶች ዓላማና ተግባር ውጭ መስራት ጀምረዋል:: የድጋፍ ድርጅቶች ዓላማና ተግባር የታወቀ ነው:: አገር ቤት ላለው ትግል ድጋፍ መስጠትና የገንዘብ አስተዋፅጽኦ ማድረግ ሲሆን በዲፕሎማሲው መስክም ስራ መስራት ነው:: በውጭ ያለው ደጋፊ የሌላ አገር ዜግነት የወሰደ ሰው የፓርቲ አባል መሆን ለምን ያስፈልገዋል? ለምንስ ይጠቅመዋል? አይመርጥ አይመረጥ:: ያለንበት አገር ሕግስ ይፈቅዳል ወይ? የሚለው ሁሉ መታየት አለበት:: ትግሉንስ ከብዙ ሺህ ኪሎሜትር ርቀት ላይ መምራትስ ይቻላልን ወይስ እንደ ኢትየጵያ ሪቪው ዌብሳይት የተግባር ሊጉን ከዚህ ሆኖ አድማ ምታ ብሎ ትእዛዝ ለማስተላለፍ ነውን?

የመጋለጡ ጉዳይ ሲያሳስባቸው አስታራቂ በማለት የሽምግልና ዘመቻም ማካሄድ ጀምረው ነበር:: ብዙም አልሰራላቸው:: በሽምግልና የሚቻል ከሆነ እነ ልደቱ አያሌውም ገና ድሮ ይታረቁ ነበር ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር:: ያ በፊት ቀረ::

አሁን የተያዘው ትልቁ የነአንዳርጋቸው ስራ የቀድሞውን የድጋፍ ድርጅቶች ማፈራረስ ነው:: ለማፍረስ ደግሞ ዋነኛ ምክንያት ኢ ዲሞክራሲያዊ ስለሆኑ መፍረስና መለወጥ አለባቸው በሚል ሰበብ በለንደንና በዋሽንግተን ዲሲ የተሰራውን የምርጫ ድራማ በሌሎችም ከተሞች ለማካሄድ እየተሯሯጡ ነው:: ዋናው ዓላማቸው ተለጣፊ ቅንጅት ለማቋቋም ነው:: አዎን ተለጣፊ ቅንጅት ለማቋቋም ነው:: የአየለ ጫሚሶ ቅንጅት፣ የተመስገን ዘውዴ ቅንጅት የአንዳርጋቸውና የብርሃነ መዋ ቅንጅት ኢንተርናሽናል:: ይህንን ወያኔያዊ ተልዕኮ ሕዝብ አውቆ በየከተማው ማጋለጥና መታገል ይኖርበታል:: ትግሉን ለመቆጣጠር ቀላሉ መንገድ ተለጣፊ ቅንጅት ማቋቋም ነው:: የልደቱ አያሌውን፣ አየለ ጫሚሶን፣ ተመስገን ዘውዴ ዓይነት አንዳርጋቸውና ጽጌና ብርሃነ መዋ ደግሞ በውጭ አገር ተለጣፊ ድርጅት ማቋቋም:: ሁሉም የወያኔ መልዕክተኞችና የውጭ ቅጥረኞች ናቸው ልዩነቱ እነዚያ በአገር ቤት እነዚህ ደግሞ በውጭው ዓለም::

**ቅንጅት አንድ ነው:: የነክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል፣ የነክብርት ወይዘሪት ብርቱካን ሜዴቅሳ፣ የነክቡር አቶ ሙሉነህ እዩኤል፣ የነክቡር ኢንጂነር ግዛቸው ሺፈራው፣ የነክቡር ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም፣ የነክቡር ዶክተር ኃይሉ አርአያና ዶክተር ያዕቆብ ኃይለማርያም፣ የነክቡር ዶክተር ብርሃኑ ነጋ የነክቡር አቶ አባይነህ ብርሃኑና የነክቡር ሻለቃ ጌታቸው መንግሥቴ እንዲሁም የሌሎቹም እውነተኛ ጀግኖች መሪዎች ቅንጅት ብቻ:: ያንን መጠበቅ ማዳን አለብን:: መሪዎቻችን እስኪፈቱልን ድርጅቱንና ትግሉን መጠበቅ አለብን:: አዎን ቅንጅት አንድ ነው:: ስሙም ተግባሩም ስራውም አንድ ብቻ ነው:: ከዚያ ውጭ አንቀበልም አናውቅም::**

ትግላችንና ድርጅታችንን ነቅተን እንጠብቅ!
ቅንጅት ያሸንፋል !
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !

ዲሴምበር 2006
የትግሉ አባልና ተቆርቋሪ

teqorquari@yahoo.com